## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 250285
ታህሳስ 30 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች ፡- ብርሃኑ አመነው**

**በዕውቀት በላይ**

**ቀነዓ ቂጣታ**

**ብርሃኑ መንግሥቱ**

**ማርታ ተካ**

**አመልካች - ፍትሕ ሚኒስቴር - ዐቃቤ ሕግ - ኤደን ጌትነት - ቀረቡ**

**ተጠሪ - ትዕግስት ሞገስ ደሳለኝ - አልቀረቡም**

መዝገቡ ተመርምሮ ከዚህ የሚከተለዉ የፍርድ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የወንጀል ክስ ክርክር አመራር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ለመዉለድ ምጥ በተያዘች ጊዜ የምጥ ስሜቷ ሳያልፍ ልጇን ለመግደል አስባ በቀን 15/06/2015ዓ/ም በግምት ከቀኑ 10:30 ሰዓት ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታዉ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጋራ ዱባ ባንክ ጀርባ ባለ መኖሪያ ቤት ዉስጥ የወለደቻትን ሴት ልጅ በእጇ አንቃ ገድላለች በማለት ከሷታል፡፡

ፍርድ ቤቱም ለተጠሪ የክስ ማመልከቻዉ እንዲደርስ አድርጎ ክሱን በንባብ ከማሰማቱና የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ወይም የእምነት ክህደት ቃል ከመስማቱ በፊት ራሱ የክስ ማመልከቻዉን በመመርመር ተጠሪ ልጇን የገደለችዉ ከወለደች በኋላ አሠሪዎቿ ሳያዩዋት ቅርጫት ዉስጥ አድርጋ ልብስ በመሸፈን በመሆኑ በተጠሪ ላይ ክስ ሊመሰረት የሚገባዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/1 ስር ሳይሆን በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡በዚህ አግባብ ክሱ ሲቀርብ ደግሞ ክሱን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለሚሆን ክሱን ለመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁጥር 296953 ላይ በቀን 08/07/2015ዓ/ም በሰጠዉ ትእዛዝ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

አመልካች ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም በመ/ቁጥር 296953 ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮና አንዲት የወለደች ሴት ከወሊድ በኋላ ለምን ያህል ጊዜ በምጥ ስሜት ልትቆይ

እንደምትችል ከጥሩነሽ ቤጂንግ ሆስፒታል ማብራሪያ እንዲሰጥ ትእዛዝ ሰጥቶ የቀረበለትን ማስረጃ መሰረት አድርጎ በቀን 30/09/2015ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ ከወሊድ በኋላ የምጥ ስሜት እንደሌለ ከቀረበዉ ማስረጃ ስለተረጋገጠ ተጠሪ መዉለዷን ለአሰሪዎቿ ሳትናገር ከወለደች በኋላ ቅርጫት ዉስጥ አድርጋዉ በላዩ ላይ ልብስ በመሸፈኑ ምክንያት የተወለደዉ ልጅ ሊሞት መቻሉንና ጉዳዩ የታወቀዉም ሆስፒታል ከሄደች በኋላ በዶክተሮች ጥቆማ ቤቱ ሲፈተሽ በመሆኑ ይግባኝ ባይ በምጥ ስሜት ሆና ወንጀሉን ፈጽማለች ብሎ ለመቀበል አይቻልም፡፡ወንጀሉ የተፈጸመዉ በምጥ ስሜት ላይ ሆና ካልሆነ ደግሞ የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 544/2 እንደሚያሳየዉ ክሱ መቅረብ ያለበት ግድያን በሚመለከቱት የወንጀል ሕጉ ድንጋጌዎች መሰረት በመሆኑና የግድያ ጉዳይም የሚታየዉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን በመዝጋቱ የተፈጸመ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በቀን 03/11/2015 ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበዉ ከላይ በተመለከተዉ መሰረት በተሰጠ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ሲሆን የአቤቱታዉ አጭር ይዘትም፡- አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረተዉ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/1 ስር የተደነገገዉን በመተላለፍ ምጥ በተያዘች ጊዜ የምጥ ስሜቷ ሳያልፍ ልጇን በእጇ አንቃ ገድላለች በሚል ነዉ፡፡በዚህ መልኩ የቀረበዉን ክስ የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሆኖ እያለ ስልጣን የለዉም መባሉ ስህተት ነዉ፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 108 እና 109 ስር በተደነገገዉ መሰረት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ መርምሮ

ተገቢ ነዉ የሚለዉን የሕግ ድንጋጌ በመጥቀስ ክስ የማቅረብ ሥልጣን የአመልካች ነዉ፡፡ዐቃቤ ሕግ የጠቀሰዉ የሕግ ድንጋጌ ከወንጀሉ ዝርዝር ጋር የማይጣጣም ከሆነ ክሱን አሻሽል ማለት ሲገባዉ መዝገቡን መዝጋቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 110 ስር የተደነገገዉን የሚቃረን በመሆኑ ስህተት ነዉ፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ከተጠየቀዉ ዳኝነት በመዉጣት የምጥ ስሜት ምንድነዉ ወደሚለዉ ተገቢ ወደአልሆነ ጭብጥ ወይም ወደፍሬ ነገር ጉዳይ ዉስጥ በመግባት የምጥ ስሜት ከወሊድ በፊት እንጂ ከወሊድ በኋላ የለም፤ እንዲሁም በክሱ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ ሊለወጥ ይገባል ወደሚል ድምዳሜ መድረሱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለት አቤቱታዉን አቅርቧል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተምርምሮ 1) በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መንግሥትን ከመወከል የወንጀል ክስ የመመስረት ሥልጣን እንዲሁም ከተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት ጋር በጣም ተቀራራቢ የሕግ ድንጋጌ ለይቶ በመጥቀስ የወንጀል ክስ የመመስረት ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ እንደሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 112 ስር ከተደነገገዉ እና ከአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(3/ሠ) ስር ከተደነገገዉ አንጻር ተገቢ መሆን አለመሆኑን? 2) ይህንን ሥልጣኑን ዐቃቤ ሕግ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጉን ፍርድ ቤቶች የማረጋገጥ ኃላፊነታቸዉን ሊወጡ የሚገባዉ የክርክሩ ሂደት በምን ደረጃ ላይ እያለ እና ምን ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነዉ? 3) ከዚህ ጋር በተያያዘም ዐቃቤ ሕግ የመሰረተዉ ክስ በፍርድ ቤቱ ዳኝነት

ሥልጣን ሥር ሆኖ እያለ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሰዉ ደንጋጌ ተገቢ አይደለም፤ ተገቢዉ ድንጋጌ ይህ ነዉ በማለት በራሱ አነሳሽነት ድንጋጌ መለወጥ የሚችልበትን አግባብና የለወጠዉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ክሱን የመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን ባለመቀበል መወሰን ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ ወይ? ከገለልተኛነት መርህ ጋር መቃረን አይሆንም ወይ? የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ ታዞ ተጠሪ የተከሰስኩበት የወንጀል ደርጊት አመልካች ባቀረበዉ ክስ ላይ እንደተመለከተዉ ደሜ እየፈሰሰ በምጥ ላይ እያለሁ የተፈጸመ ነዉ በማለት በቃል አስረድታለች፡፡

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የተገለጸዉ የክሱን ይዘት፣ የግራ ቀኙን ክርክር እና የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ የሚመለከት ሲሆን እኛም ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን ጭብጦች በመያዝ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

*በመጀመሪያም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠዉ ዉሳኔ መንግሥትን በመወከል የወንጀል ክስ የመመስረት ሥልጣን እንዲሁም ከተፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት ጋር በጣም ተቀራራቢ የሕግ ድንጋጌ ለይቶ በመጥቀስ*

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

*የወንጀል ክስ የመመስረት ሥልጣን የዐቃቤ ሕግ እንደሆነ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 112 እና ከአዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(3/ሠ) ስር ከተደነገገዉ አንጻር ተገቢ መሆን አለመሆኑን?* በሚል የያዝነዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም በአገራችን በተዘረጋዉ የወንጀል ፍትህ አስተዳደር ሥርዓት መሰረት ሕገ-ወጥነቱና አስቀጪነቱ በሕግ የተደነገገዉን የወንጀል ድርጊት መፈጸሙ ወይም በሕግ ወንጀል ነዉ ተብሎ የደነገገዉን ድርጊት ወይም አል ድርጊት ሕጋዊ፣ ግዙፋዊ እና ሞራላዊ ፍሬ ነገሮችን በአንድነት በተሟላ መልኩ መፈጸሙ በፍርድ ቤት የተረጋገጠበት ወንጀል ፈጻሚ በወንጀል ሕጉ አግባብ መቀጣት ይገባዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ለማቋቋም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 943/2008 አንቀጽ 6(3/ሠ) እና በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 107 እና 109/1 ስር እንደተደነገገዉ የፌዴራልን መንግሥት በመወከል በወንጀል ጉዳዮች ክሱ የሚቀርብበትን ፍርድ ቤት ለይቶ በወንጀል ፈጻሚዉ ላይ ክስ መስርቶ እንዲከራከር ሥልጣን የተሰጠዉ ለቀድሞዉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ወይም ለአሁን ፍትህ ሚኒስቴር ነዉ፡፡

ዐቃቤ ሕግ በወንጀል የክስ ማመልከቻ ላይ የሚጠቅሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ተከሳሹ ፈጸመ የተባለውን ተግባር ወንጀል ከሚያደርገው ሕግ አነጋገር ጋር በጣም የተቀራረበ መሆን እንደሚገባው በወ/መ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁጥር እና 111(1/መ) እና 112 ስር ተደንግጓል፡፡በዚህ መልኩ የተደነገገበት ምክንያት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት ከሳሽ አቃቤ ሕግ በክሱ በሚጠቅሰዉ ድንጋጌ የተመለከተዉ የወንጀል ማቋቋሚያ አላባዎች (ፍሬ ነገሮች) ተሟልተው መገኘታቸውን ለማስረዳት እንዲያስችለውና ተከሳሹም ክሱን ከተጠቀሰበት ድንጋጌ አላባዎች አንጻር ጭምር በመከራከር መከላከል እንዲችል ለማድረግ እንደሆነ

ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ ይቻላል፡፡ክሱን በዚህ አግባብ አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ በሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠዉ ለዐቃቤ ሕግ ሲሆን ይህንን ሥልጣኑን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረጉን ኃላፊነቱን ደግሞ መወጣቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት ደግሞ በየደረጃዉ ያሉ ፍርድ ቤቶች ነዉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ይህንን ሥልጣኑን ዐቃቤ ሕግ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ አለማድረጉን ፍርድ ቤቶች የማረጋገጥ ኃላፊነታቸዉን ሊወጡ የሚገባዉ የክርክሩ ሂደት በምን ደረጃ ላይ እያለ እና ምን ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነዉ? በሚል የያዝነዉን ጭብጥ ስንመረምር ስለወንጀሉ ወይም ስለወንጀሉ አስፈላጊ ዝርዝር በክሱ ማመልከቻ ላይ ስህተት ተደረጓል ወይም አስፈላጊ ዝርዝር ሳይጠቀስ ቀርቷል በሚል ክሱን ዋጋ ማሳጣት እንደማይቻል፤ስህተቱ ወይም ሳይጠቀስ የቀረዉ አስፈላጊ ነገር ከሆነ ወይም ተከሳሹን የሚያሳስት የሆነ እንደሆነ ወይም ተከሳሹን ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ ወይም በዚህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል መስሎ በታየ ጊዜ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማንኛዉም የክርክር ደረጃ ፍርድ ቤቱ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተከራካሪ ወገኖች ማመልከቻ ሲቀርብ ክሱ እንዲሻሻል፣እንዲለወጥ ወይም

ሳይጠቀስ የቀረዉ እንዲጨመር ማዘዝ እንደሚችል በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 118 እና 119 ስር ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡

በተጨማሪም ፍርድ ቤቶች ክርክር ሲሰሙ፣ ማስረጃ ሲመረምሩና ሲመዝኑ እንዲሁም ዳኝነት በተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ዉሳኔ ሲሰጡ ከማንኛዉም ተጽዕኖ ነጻ በመሆን ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ ሳይመሩ የወንጀል ሕጉን ግብ፣ ዓላማዎችና መርሆዎች ባከበረ እንዲሁም መንግሥትን በመወከል የወንጀል ክስ እንዲመሰርት፣ ተከራክሮ በሕግ አግባብ እንዲያስቀጣ በሕግ ሥልጣን የተሰጠዉን የአመልካችን ሥልጣንና ተግባር ባከበረ፣ የተጎጂዉን እና የከሳሹን መብቶች ባስከበረ አኳኋን የቀረበላቸዉን ክስ፣ክርክር እና ማስረጃዎችን በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት ተከትለዉ በመስመትና በከመሰረታዊ ሕግ አንጻር ጭምር በመመርመር በገለልተኛነት እና በሙሉ ነጻነት የዳኝነት ተግባራቸዉን የማከናወን ግዴታ እና ኃላፊነት እንዳለባቸዉ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 9(1፣2፣ እና 4)፣13፣20፣37፣79(2 እና 3) ፣ከወንጀል ሕጉ ታላቅ ክፍል እና ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት አመልካች በሚመሰርተዉ የወንጀል ክስ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 112 ስር በተደነገገዉ መሰረት ተከሳሹ የፈጸመዉን ድርጊት ወንጀል የሚያደርገዉን በጣም ተቀራራቢ ድንጋጌ ለይቶ የመጥቀስ ግዴታ አለበት፡፡በመርህ ደረጃ አመልካች ይህንን ግዴታዉን በአግባቡ ይወጣል ተብሎ ይገመታል፡፡ነገር ግን ፍርድ ቤት አመልካች ይህንን ግዴታዉን በአግባቡ መወጣቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ፍርድ ቤት አመልካች በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ተገቢ ድንጋጌ አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ እንዲደርስ እና በዚህ ምክንያት ክሱ እንዲሻሻል ወይም እንዲለወጥ ሊያዝ የሚችልባቸዉን

ዋና ዋና ምክንያቶች ለመጥቀስ ያህል፡- 1) በክሱ የተገለጸዉ የወንጀል ድርጊት በክሱ በተጠቀሰዉ ግዙፋዊ ፣ሞራላዊ እና ሕጋዊ አላባዎች ጋር የማይጣጣም የሆነ እንደሆነ፣2) በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና ተከሳሹ የፈጸመዉ የወንጀል ድርጊት ነዉ ተብሎ በክሱ የተገለጸዉ ድርጊት የማይጣጣም ከመሆኑ የተነሳ ተከሳሹን የሚያሳስት የሆነ እንደሆነ ወይም ተከሳሹን ያሳሳተ መስሎ ሲታይና በዚህ ምክንያት የተከሳሹ ክሱን የመከላከል መብት የሚነካ ሲሆን፣3) ዐቃቤ ሕግ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ነዉ ብሎ በክሱ ላይ ከገለጸዉ ድርጊት ጋር በግልጽ የማይጣጣም የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የጠቀሰዉ የተከሳሹን የዋስትና መብት ለማስከልከል ነዉ የሚያስብል በሕግ እና በክሱ ላይ በተገለጸ ፍሬ ነገር ላይ የተመሰረተ ምክንያት ሲገኝ እና 4) በሌላ አሳማኝ ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል መስሎ በታየ ጊዜ ነዉ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከላይ የተጠቀሱትን ምክንያቶች መሰረት በማድረግ ክሱ እንዲሻሻል ማድረግ የሚቻለበት የክርክር ሂደት ደረጃ እንደየምክንያቶቹ ሁኔታ እና ለማስከበር ከሚፈለገዉ መብት ባህሪይ አንጻር ሊለያይ ይችላል፡፡በዚህ መሰረት በክሱ ላይ የተገለጸዉ የወንጀል ድርጊት በማስረጃ ቢረጋገጥ ተከሳሹ በክሱ በተጠቀሰዉ ድንጋጌ ስር ክሱን እንዲከላከል ሊታዘዝ አይችልም የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻል ሲሆን ወይም በክሱ ከተጠቀሰዉ የሕግ ድንጋጌ ላይ የወንጀል ማቋቋሚያ አላባዎች እና/ወይም ማክበጃ ምክንያቶች ሆነዉ ከተደነገጉት አንጻር ለአብነት ለመጥቀስ ያህል ከወንጀል ፈጻሚዉ የሥልጣን ደረጃ፣ ተከሳሹ ወይም ሶስተኛ ወገን ካገኘዉ ጥቅም እና ከደረሰዉ ጉዳት አንጻር ሲታይ ተገቢ ያልሆነ ድንጋጌ ተጠቅሷል የሚል ድምዳሜ ላይ በማያከራክር ሁኔታ መድረስ የሚቻል ሲሆን በክሱ በተጠቀሰዉ ድንጋጌ ስር ክሱን ተከሳሹ እንዲከላከል ላይታዘዝ የሚችልበት ዕድል ሰፊ ስለሚሆን ዐቃቤ ሕግም በክሱ ላይ ተገቢዉን ድንጋጌ ጠቅሶ ክሱን ካሻሻለ በኋላ ምስክሮቹን አቅርቦ እንዲያሰማ ለማድረግ፣ እንዲሁም ተከሳሹ ክሱን መከላከል የሚጀምረዉ የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ በመጠየቅ እንደመሆኑ ተሻሽሎ በቀረበ ክስ ላይ ከተጠቀሰዉ ትክክለኛ ድንጋጌ አንጻር ተከሳሹ ይህንን መብቱን በአግባቡ እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፣ ይህንን የመሰለ የክርክሩን ሂደት ወደኋላ የሚመልስ (የሚያጓትት) ጉድለት ከወዲሁ በማስተካከል የተፋጠነ ፍትህ መስጠት ይቻል ዘንድ፣ በተጨማሪም በክስ ማመልከቻዉ ላይ የወንጀል ፈጻሚዉ የሥልጣን ደረጃ ነዉ ተብሎ ከተገለጸዉ፣ ተገኝቷል ተብሎ ከተጠቀሰዉ ጥቅም እና/ወይም የደረሰ ጉዳት ነዉ ተብሎ ከተገለጸዉ አንጻር ሲታይ ተገቢ ያልሆነ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ አለአግባብ በመጠቀሱ ምክንያት የተከሳሹ የዋስትና መብት ተከልክሎ በተከሳሹ ላይ ሊተካ የማይችል ጉዳት እንደሚደርስ ማረጋገጥ በተቻለ ጊዜ፤ በአጠቃላይ ለክርክሩ ዉጤታማ አመራር፣ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠትና የተከሳሹን የመከላከል እና የዋስትና መብቶች በማስጠበቅ የሕገ ምንግሥቱ አንቀጽ 19(1 እና 6)እና 20(2 እና 4) የተደነገገዉ ተግባራዊ እንዲሆን ለማድረግ ተጠቃሾቹን ምክንያቶች እንደመሰረታዊ ምክንያቶች በመቁጥር በተቻለ መጠን የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች

ከመሰማታቸዉ በፊት ዘግይቶ ከታወቀም እንደነገሩ ሁኔታ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ እና ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት ዐቃቤ ሕግ ክሱን እንዲያሻሽል ወይም እንዲለዉጥ ሊታዘዝ ይችላል፡፡

በመቀጠል ዐቃቤ ሕግ የመሰረተዉ ክስ በፍርድ ቤቱ ዳኝነት ሥልጣን ሥር ሆኖ እያለ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሰዉ ደንጋጌ ተገቢ አይደለም፤ ተገቢዉ ድንጋጌ ይህ ነዉ በማለት በራሱ አነሳሽነት ድንጋጌ መለወጥ የሚችልበትን አግባብና የለወጠዉን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ክሱን የመዳኘት ሥልጣን የለኝም በማለት ክሱን ባለመቀበል መወሰን ሥነ ሥርዓታዊ ነዉ ወይ? ይህም ከገለልተኛነት መርህ ጋር መቃረን አይሆንም ወይ? በሚል የያዝነዉን ጭብጥ መርምረናል፡፡ ፍርድ ቤት በሕግ በተሰጠዉ የዳኝነት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሥልጣኑ ሥር ሆኖ የቀረበዉን ክስ ተቀብሎ ዳኝነት የመስጠት የሕግ ግዴታ ያለበት መሆኑ የሚታወቅ ነዉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በክሱ የተገለጸዉን የወንጀል ደርጊት የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ተሰምቶ ሳይረጋገጥ በክስ ማመልከቻዉ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ ተገቢ ነዉ ወይም አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የማይቻልበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የቀረበዉ ክስ በዳኝነት ሥልጣኑ ስር እስከሆነ ድረስ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት በክሱ ላይ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና በተከሳሹ የተፈጸመ ነዉ ተብሎ በክስ ማመልከቻዉ ላይ የተገለጸዉ የወንጀል ዝርዝር አፈጻጸም ከድንጋጌዉ ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ የቀረበዉን የክስ ማመልከቻ በንባብ በማሰማት የተከሳሹን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና/ወይም የእምነት ክህደት ቃል በመስማት ክሱን መስማት መጀመርና የሥነ ሥርዓት ሕጉን ተከትሎ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች በመስማት ተከሳሹ ወንጀሉን የፈጸመ መሆን አለመሆኑን፤ተከሳሹ ወንጀል ስለመፈጸሙ ተረጋግጦ ከሆነም የተረጋገጠዉን ድርጊት ወንጀል የሚያደርገዉን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በመለየት ተከሳሹ ክሱን መከላከል የሚገባዉ መሆን አለመሆኑን እና ክሱን ሊከላከል የሚገባዉ በክሱ ላይ በተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ መሰረት ከሆነም ይህንኑ በመግለጽ አሊያም በክሱ የተጠቀሰዉን ድንጋጌ በመለወጥ ተከሳሹ ክሱን እንዲከላከል ማዘዝ እንዳለበት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 113/2 እና 142/2 ስር የተደነገገዉ ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም ዐቃቤ ሕግ የመሰረተዉ ክስ በፍርድ ቤቱ ዳኝነት ሥልጣን ሥር ሆኖ እያለ ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የጠቀሰዉ ደንጋጌ ተገቢ አይደለም፤ የዐቃቤ ሕግን ምስክሮች ሰምቶ የተፈጸመዉን የወንጀል ምንነት ባላረጋገጠበት ተገቢዉ ድንጋጌ ይህ ነዉ በማለት በራሱ አነሳሽነት በክሱ የተጠቀሰዉ ድንጋጌ ተለዉጦ ክስ ሊቀርብ ይገባል፤ድንጋጌዉ ሲለወጥ ደግሞ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን አይኖረኝም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች *"…ተጠሪ መዉለዷን ለአሰሪዎቿ ሳትናገር ከወለደች በኋላ ቅርጫት ዉስጥ አድርጋዉ በላዩ ላይ ልብስ በመሸፈኗ ምክንያት የተወለደዉ ልጅ ሊሞት መቻሉንና ጉዳዩ የታወቀዉም ሆስፒታል ከሄደች በኋላ በዶክተሮች ጥቆማ ቤቱ ሲፈተሽ በመሆኑ ተጠሪ በምጥ ስሜት ሆና ወንጀሉን ፈጽማለች ብሎ ለመቀበል አይቻልም፡፡…"* የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱት የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል ሳይቀበሉ እና ዐቃቤ ሕግ ምስክሮቹን አቅርቦ አሰምቶ ማስረጃዉ ተመዝኖ በተጠሪ የተፈጸመዉ ወንጀል ባልተረጋገጠበት በመሆኑ ከዳኝነት አካል የሚጠበቀዉን መሰረታዊ የገለልተኛነት መርህ የሚጥስ ከመሆኑም በተጨማሪ በፍርድ ቤቶቹ በተጠቀሰዉ አግባብ የተደረሰበት ድምዳሜ የወንጀል ክስ የቀረበበት ሰዉ በፍርድ ጥፋተኛነቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ በፍርድ ሂደት ባለበት ጊዜ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዳለዉ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 20/3 ስር ጥበቃ የተደረገዉን መብት የሚሸራርፍ ስለሆነ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

እንዲሁም አመልካች በተጠሪ ላይ በመሰረተዉ ክስ ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/1 ስር የተደነገገዉን መተላለፏን በክሱ ገልጿል፡፡ የወንጀሉን ዝርዝር አፈጻጸም በተመለከተም *"...ተጠሪ በቀን 15/06/2015ዓ/ም በግምት ከቀኑ 10:30 ሰዓት ሲሆን በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ልዩ ቦታዉ ጋራ ዱባ ባንክ ጀርባ ባለ መኖሪያ ቤት ዉስጥ ለመዉለድ ምጥ በተያዘች ጊዜ የምጥ ስሜቷ ሳያልፍ ልጇን ለመግደል አስባ የወለደቻትን ሴት ልጅ በእጇ አንቃ በመግደሏ ተከሳለች፡፡"* በሚል ከሷታል፡፡በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/1 ስር የተደነገገዉም "አንዲት እናት ለመዉለድ ምጥ በተያዘች ጊዜ ወይም የምጥ ስሜትዋ ሳያልፍ አስባ ልጅዋን የገደለች እንደሆነ፤እንደነገሩ ሁኔታ በቀላል እሥራት ትቀጣለች፡፡"የሚል ነዉ፡፡ይህ ድንጋጌ ተጠቅሶበት የሚቀርብ የወንጀል ክስ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ አንደኛ አባሪ ሰንጠረዥ መሰረት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡የክሱ ይዘት በግልጽ እንደሚያሳየዉ አመልካች በተጠሪ የተፈጸመ ወንጀል ነዉ ተብሎ ከተገለጸዉ የወንጀል ድርጊት ጋር በጣም ተቀራራቢ ድንጋጌ በመሆኑ አመልካች ክሱን ያቀረበዉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 112 ስር በተደነገገዉ አግባብ ነዉ፡፡

ከላይ የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ ድርጊቱን የፈጸመችዉ ለመዉለድ ምጥ በተያዘች ጊዜ ሳይሆን ወይም የምጥ ስሜትዋ ካለፈና ከወለደች በኂላ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ የሚቻለዉ የክስ ማመልከቻዉ ለተጠሪ ተነቦላት ተጠሪ ወንጀሉን አልፈጸምኩም፤ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዳ የምትከራከር ከሆነ የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ከተሰማ እና ማስረጃ ከተመዘነ በኂላ ነዉ፡፡ነገር ግን የስር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ራሱ የክስ ማመልከቻዉን በመመርመር "...ተጠሪ ልጇን የገደለችዉ ከወለደች በኂላ አሠሪዎቿ ሳያዩዋት ቅርጫት ዉስጥ አድርጋ ልብስ በመሸፈን በመሆኑ... "በማለት ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ የተጠቀሰዉን የወንጀል ሕግ ድንጋጌ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 544/2 መሰረት ተገቢዉን ድንጋጌ በመጥቀስ መለወጥ አለበት፤ይህንን ሲያደርግ ደግሞ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለሚሆን ሥልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን መዝጋቱ ከላይ እንደገለጽነዉ በክሱ በተጠሪ ተፈጸመ የተባለዉ የወንጀል ድርጊትና በክሱ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ የተጣጣመ ነዉ እንጂ በክሱ የተጠቀሰዉ የሕግ ድንጋጌ ተፈጸመ ከተባለዉ ድርጊት ጋር በጣም ተቀራራቢ አይደለም፤ ይህም በመሆኑ

ምክንያት ተጠሪን አሳስቷል፤ወይም የመከላከል መብቷን የሚያጣብብ ሆኗል ቢባል እንኳን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 111(1/መ) ፣ 112፣ 118 እና 119 መሰረት ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል እንጂ ክሱ ባልተሻሻለበት የቀረበዉም ክስ በሥልጣኑ ስር ሆኖ እያለ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተጠሪን የእምነት ክህደት ቃል እና የዐቃቤ ሕግ ምስክሮች ሰምቶ የተፈጸመዉን የወንጀል አይነት ሳያረጋግጥ ሥልጣን የለኝም በማለት የክስ መዝገቡን መዝጋቱ መሰረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ጉድለት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ስህተት ነዉ፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተዉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይግባኙ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም በማለት የክስ መዝገቡን የዘጋበት አግባብ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም በሚል የቀረበለትን ይግባኝ ተቀብሎ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍርድ ቤት ከላይ በተመለከተዉ መሰረት የፈጸመዉን ስህተት ማረም ሲገባዉ በክስ ማመልከቻዉ ላይ የተጠቀሰዉ የወንጀል ሕግ ድንጋጌ እና በተጠሪ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ነዉ ተብሎ በክሱ ከተገለጸዉ አንጻር በማየት በክሱ ከተገለጸዉ የወንጀል ደርጊት አፈጻጸም ጋር የሚጣጣም አይደለም ባላለበት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ጉድለት የለበትም በማለት ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ እንዲሁም ገና የተጠሪ የእምነት ክህደት ቃል እና የአመልካች ምስክሮች ባልተሰሙበት ተጨማሪ ማስረጃ አስቀርቦ መርምሮ ተጠሪ ወንጀሉን የፈጸመችዉ ከወለደችና የምጥ ስሜቷ ካለፈ በኋላ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ መድረሱም የቀረበለትን ይግባኝ ቅሬታ መሰረት ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ስለወንጀል ክስ አሰማማም፣ ስለተጨማሪ ማስረጃ አቀራረብ እና የይግባኝ ክርክር ስለሚመራበት አግባብ በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ስለሆነም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተወስኖ በከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸናዉ ዉሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ እና ለ) እና 10(1/ሐ እና መ) ስር በተደነገገዉ መሰረት ሊታረም የሚገባዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሆነ ተከታዩን ወስኗል፡፡

## ዉሳኔ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 296953 ላይ በቀን 08/07/2015ዓ/ም የሰጠዉ ትእዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 296953 በቀን 30/09/2015ዓ/ም የሰጠዉ ዉሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/1 መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ጉዳዩን ያላዩት ዳኛ ወይም ችሎት መዝገቡን አንቀሳቅሶ በሥነ ሥርዓት ሕጉ አግባብ ክሱን በመስማት እና ክርክሩን በመምራት ተገቢዉን እንዲወስን ጉዳዩ በሰበር ሥነ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9/2 መሰረት ተመልሶለታል፡፡

## ትዕዛዝ

1. በዉሳኔዉ መሰረት እንዲፈጽም የዉሳኔዉ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤት ይተላለፍ፡፡ የዉሳኔዉ ግልባጭ ለግራ ቀኙም ይሰጣቸዉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !